特定非営利活動法人 Japan Association for Refugees
難民支援協会

To Those アムハラ語/ 2005年8月作成/2013 年 2 月更新

# የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ለሚያመለከቱ ሰዎች የሚሰጡ ምክሮች

**በጃፓን የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ (Refugee Application) የሚመለከት መግለጫ እና ለጥገኝነት እወቅና ጥያቄ አመልካቾች የሚሰጡ ምክሮች**

JAR
〒160-0004 ቶክዮ-ቶ ሺንጁኩ-ኩ ዮትሱያ 1-7-10 ዳይሳን ሺካኩራ ቢሩ ሮክ ካይ (= 6ኛ ፎቅ)
ስልክ ０１２０－４７７－４７２（አመልካቾች በነጻ መደወል ይችላሉ）
０３－５３７９－６００３（ለአመልካች ብቻ）
ፋክስ ０３－５３７９－６００２
ኢ. ሜይል: info@refugee.or.jp
http://www.refugee.or.jp

## ማውጫ

Ⅰ መቅድም～"ሬፉጂ (Refugee)" ማለት ምንድን ነው? ..... 3

Ⅱ ከማመልከት በፊት ማወቅ የሚያስፈልግዎ ነገር ..... 4

1. በጃፓን የጥገኝነት እውቅና ሥርዓት ..... 4

1) አጠቃላይ

2) የጥገኝነት እውቅና ካገኙ በኋላ የሚሰጡዎ መብቶች

3) እውቅና ያገኙት ጥገኞች ቁጥር

4) የፕሮሴሶች አጭር መግለጫ

①የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ማመልከት

②የሬፉጂ መርማሪ ቃለ መጠየቅ እና ውሳኔው

③ይግባኝ መጠየቅ

④ይግባኝ ፕሮሴስ በተመለከተ የሚካሄድ ንግግርና ቃለ መጠይቅ እና ውሳኔው

⑤አስተዳደራዊ ክስ(የፍርድ ቤት ምርመራ)

2. የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ መሰረታዊ ነገሮች ..... 7

1) ስቃይ ማለት ምንድን ነው?

2) የስቃይ ምክንያት

3) ስቃይ ማስረዳት

3. የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ለማመልከት የሚዘጋጁ ዶክሜንቶች ..... 8

1) የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ማመልከቻ ፎርም ማግኘት

2) የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ማመልከቻ ፎርም መሞላት

3) የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ማመልከቻ ፎርም የሚገባበት ቦታ

4) የግል መግለጫ (Personal Statement) መጻፍ

5) ሌሎች ማስረጃዎች

4. ጊዜያዊ ቆይታ (Provisional Stay, Karitaizai) ..... 11

5. በሰብአዊ ርህራሄ ምክንያት የሚሰጥ ልዩ መኖሪያ ፈቃድ ..... 11

6. ከጃፓን አገር የማስወጣት ፐሮሴስ (Deportation, Taikyo Kyosei Tetsuzuki) 12

1) የትልልፍ ምርምርና ምርመራ

2) ጊዜያዊ መልቀቂያ ማመልከት እና ጊዜያዊ መልቀቅ (Kari Homen)

3) ከዚያ በኋላ የሚደረግ ፐሮሴስ

Ⅲ ጥያቄና መልስ 14

ተጨማሪ I የጃፓንኛ ቃላት ፍች ዝርዝር 18

ተጨማሪ II አድራሻ ወዘተ 19

# I መቅድም ～ "ሬፉጂ (Refugee)" ማለት ምንድን ነው?

"ሬፉጂ Refugee" ማለት ምን እንደሆነ ከዚህ በታች እንደተጻፈ ተገልጿል (በ1951 በወጣ ሬፉጂነትን የሚመለከት ስምምነት (Refugee Convention) 1. A(2)) ።

《በዘር፤ በሃይማኖት፤ በዜግነት፤ የሆነ ማኅበራዊ ድርጅት አባል በመሆን ወይም በፖለቲካ አመለካከት ምክንያት ሊሰቃይ የሚችልበት በቂ ምክንያት ባለው ፍርሃት ምክንያት ከዜግነቱ አገር ውጭ የሚገኝ ሆኖ ከዜግነቱ አገር ጥበቃ መቀበል የማይችል ወይም በዚህ ፍርሃት ምክንያት ከዜግነቱ አገር ጥበቃ ለመቀመል የማይፈልግ፤ እና በዚህ ችግር ምክንያት ይኖር ከነበረባት አገር ውጭ የሚገኝ ዜግነት የሌለው ሆኖ ይኖር ወደነበረባት አገር መመለስ የማይችል ወይም በዚህ ፍርሃት ምክንያት ይኖር ወደነበረባት አገር ለመመለስ የማይፈልግ ሰው》

(ከስሩ ያሰመረው JAR ነው)

በስምምነቱ መሰረት የጥገኝነት እውቅና ለማግኘት 4 ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላት አለብዎ ።

(1) ካገርዎ ውጭ መሆን

(2) ስቃይ ሊደርስብኝ ይችላል የሚሉበት በቂ ምክንያት ያለው ፍርሃት መኖር

(3) ፍርሃቱ በዘር፤ በሃይማኖት፤ በዜግነት፤ የሆነ ማኅባራዊ ድርጅት አባል በመሆን፤ ወይም በፖለቲካ አመለካከት ምክንያት መሆን

(4) ያገርዎ ጥበቃ ማግኘት የማይችሉ ወይም በፍርሃቱ ምክንያት የማይፈልጉ መሆን

**ማን ነው የጥገኝነትን እውቅና የሚፈቅድልዎ?**

የጥገኝነትን እውቅና የሚፈቅድልዎ ሃላፊነት ያለው የጃፓን መንግስት ነው። ከዚህ በታች ስለጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ማመልከት (Refugee Application) ፐሮሴስ እንገልጻለን።

# Ⅱ ከማመልከት በፊት ማወቅ የሚያስፈልግዎ ነገር

## 1. በጃፓን የጥገኝነት እውቅና ሥርዓት

### 1) አጠቃላይ

ጃፓን በ1981 በሬፉጂነት የሚመለከት ስምምነት (Refugee Convention) ፈረመች（ከ1982 ጀምሮ ተግባራዊ ሆኗል)። የጃፓን ሕጎችን ስንመለከት የኢሚግሬሽን ቁጥጥርና የጥገኝነት እውቅና ሕግ (the Immigration Control and Refugee Recognition Act፤ ከዚህ በታች <<የኢሚግሬሽን ሕግ>> ብለን እንጠራዋለን) ነው የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ፕሮሴስ የሚገልጸው።




★የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ፕሮሴስ በተመለከተ ኢሚግሬሽን ባዘጋጀ መጽሔት <<የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ፕሮሴስ መምሪያ>>（ጃፓንኛ፣ እንግሊዝኛ፣ ቻይንኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ እስፓንኛ፣ አረብኛ፣ ቱርክኛ፣ ምያማርኛ፣ ኡርዱኛ፣ ፋርስኛ፣ ሩሲያኛ፣ ኰሪያኛ፣ ዳርኛ፣ ፓሽትኛ）ላይ ማብራሪያ አለ።

### 2) የጥገኝነት እውቅና ካገኙ በኋላ የሚሰጡዎ መብቶች

የጥገኝነት እውቅና ማግኘት ከቻሉ ከዚህ በታች የተፃፉት ጥበቃና ጥቅም ይሰጡዎታል።

- ወደአገርዎ አለመላክ፤ ወደአገርዎ እንዲመለሱ አይደረግም።
- የመኖሪያ ፈቃድ መስጠት፤ ቪዛ አልቆ（ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ）የሚኖሩ፤ ትክክል ባልሆነ መንገድ（ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ）የገቡ ቢሆኑም ወይም የመኖሪያ ፈቃድዎ ያጭር ጊዜው ቢሆንም ባብዛኛው ጊዜ ለረጅም ጊዜ ለመኖርና ለመሥራት የሚያስችል የነዋሪነት ፈቃድ ይሰጥዎታል።
- የሬፉጂ ጉዞ መታወቂያ፤ እንደፓስፖርት የሚያገለግል መታወቂያ እንዲሰጥዎ ለማመልከት ይችላሉ። በዚህ በመጠቀም ወደውጭ አገር መጓዝ ይችላሉ።
- የተለያዩ መብቶች መሰጠት፤ የጤና ኢንሹራንስ ለመግባት እና በገንዘብ ሲቸገሩ እርዳታ (Seikatsu Hogo) ለመጠየቅ ይችላሉ። ሌላው ደግሞ በሥራም ሆነ በትምህርት ከዜጐቻችን (በጃፓን ከሚኖሩ ጃፓናውያን) ጋር እኩል የሆነ አቀባበል ለማግኘት ይችላሉና ቋሚ ነዋሪነት ፈቃድ ለማግኘት የሚሟላ ቅድመ ሁኔታም ቀላል ይሆናል;;

3）**እውቅና ያገኙት ጥገኞች ቁጥር**（ከፍትህ ሚኒስቴር ኢምግሬሽን ስታቲስቲክስ）

| ዓመት | አመልካች | ይግባኝ | የተፈቀደላቸው | ያልተፈቀደላቸው（ለመጀመሪያ） | ያቆሙ（ለመጀመሪያ） | በሰብአዊ ርህራሄ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1982 | 530 | 22 | 67 | 40 | 59 | |
| 1983 | 44 | 7 | 63 | 177 | 23 | |
| 1984 | 62 | 55 | 31 | 114 | 18 | |
| 1985 | 29 | 23 | 10 | 28 | 7 | |
| 1986 | 54 | 5 | 3 | 5 | 5 | |
| 1987 | 48 | 29 | 6 | 35 | 11 | |
| 1988 | 47 | 53 | 12 | 62 | 7 | |
| 1989 | 50 | 26 | 2 | 23 | 7 | |
| 1990 | 32 | 23 | 2 | 31 | 4 | |
| 1991 | 42 | 10 | 1 | 13 | 5 | 7 |
| 1992 | 68 | 36 | 3 | 41 | 2 | 2 |
| 1993 | 50 | 28 | 6 | 33 | 16 | 3 |
| 1994 | 73 | 33 | 1 | 41 | 9 | 9 |
| 1995 | 52 | 39 | 1(1) | 32 | 24 | 3 |
| 1996 | 147 | 35 | 1 | 43 | 6 | 3 |
| 1997 | 242 | 41 | 1 | 80 | 27 | 3 |
| 1998 | 133 | 159 | 15(1) | 293 | 41 | 42 |
| 1999 | 260 | 158 | 13(3) | 177 | 16 | 44 |
| 2000 | 216 | 61 | 22 | 138 | 25 | 36 |
| 2001 | 353 | 177 | 24(2) | 316 | 28 | 67 |
| 2002 | 250 | 224 | 14 | 211 | 39 | 40 |
| 2003 | 336 | 226 | 6(4) | 298 | 23 | 16 |
| 2004 | 426 | 209 | 9(6) | 294 | 41 | 9 |
| 2005 | 384 | 183 | 31(15) | 249 | 32 | 97 |
| 2006 | 954 | 340 | 22(12) | 389 | 48 | 53 |
| 2007 | 816 | 362 | 37(4) | 446 | 61 | 88 |
| 2008 | 1599 | 429 | 40(17) | 791 | 87 | 360 |
| 2009 | 1388 | 1156 | 22(8) | 1703 | 123 | 501 |
| 2010 | 1202 | 859 | 26(13) | 1336 | 93 | 363 |
| 2011 | 1867 | 1719 | 7(14) | 2002 | 110 | 248 |
| 2012 | 2545 | 1738 | 5(13) | 2083 | 110 | 112 |
| ድምር | 14299 | 8465 | 503(113) | 11523 | 1107 | 2106 |

ማሳሳቢያ፤ ቅንፍ ውስጥ ያሉት ቅጥሮች በይግባኝ ፕሮሴስ ላይ የተፈቀደላቸው ሲሆን በ<<ድምር>> ላይ ያልተደመሩ ናቸው።

## 4) የፕሮሴሶች አጭር መግለጫ

### ① የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ማመልከት

የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ማመልከት የሚችሉበትን ወቅት የሚገድብ ደንብ የለም። መኖሪያ ፈቃድ እያለዎ የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ የሚያመለክቱ ከሆነ መኖሪያ ፈቃድ የማሳደስ ወይም የመቀየር ፕሮሴስ በመፈጸም የቆይታዎ ጊዜ ይራዘማል። መኖሪያ ፈቃድ ከሌላዎ የጊዜያዊ መኖሪያ ፈቃድ (Kari Taizai) ምርመራ ይካሄዳል። ጃፓን ከገቡበት ቀን (በጃፓን እያሉ ሬፉጂ የሚሆኑበት ምክንያት የተፈጠረ ከሆነ እሱን ካወቁበት ቀን) ጀምሮ በ6 ወር ውስጥ የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ማመልከቻ ፎርም ማስገባት የሚያስፈልግ መሆንን ወዘተ ይጠንቀቁ (ስለዝርዝሩ ምዕራፍ 4ን ይመልከቱ)።

### ② የሬፉጂ መርማሪ ቃለ መጠየቅ እና ውሳኔው

የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ካመለከቱ በኋላ የኢሚግሬሽን ሠራተኛ የሆነ የሬፉጂ መርማሪ ለቃለ መጠይቅ እንዲቀርቡ ይጠራዎታል። ቃለ መጠይቅ ከአንድ እስከተወሰነ ጊዜ ይካሄዳል። ዐዋቂ ከሆኑ ከጠበቃዎ ከጓደኛዎ ወዘተ ጋር በቃለ መጠይቅ መገኘትዎ አይፈቀድልዎትም። ከዚያ በኋላ የጥገኝነት እውቅና ያግኙ አያግኙ ውሳኔው ይነገርዎታል እንጂ ለቃለ መጠይቅ ከመጠራትዎ ውሳኔ እስከሚነገርዎ ድረስ ለተወሰነ ወራት ሊፈጅብዎም ይችላል። በቃለ መጠይቅ የተናገሩት ነገር በ statement ወረቀት ላይ ይፃፋል። ቃለ መጠይቅ ካለቀ በኋላ በወረቀቱ ላይ እንዲፈርሙ ይጠየቃሉ። ባስተርጓሚ አማካይነት የተፃፈው ነገር በደንብ ተረድተው ስህተት አለመኖርን አረጋግጥው ይፈርሙ።

### ③ ይግባኝ መጠየቅ

የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ መልስ <<አልተፈቀደልዎትም>> ከሆነ ይግባኝ ለመጠየቅ ይችላሉ። በይግባኝ ማመልከቻ ፎርም ላይ የሚቃውሙበትን ምክንያት ፅፈው የሚቃወሙበትን ምክንያት ከሚያስረዳ ዶክሜንት ጋር አያይዘው ለፍትህ ሚኒስትር በማቅረብ ነው የሚጠይቁት። ምክንያትንና ማስረጃን በኋላ በተጨማሪ ማስገባት ይችላሉ እንጂ የይግባኝ ማመልከቻ ፎርም ራሱ የጥገኝነት እውቅና እንዳልተገኘ  ካወቁበት ቀን ጀምሮ 7 ቀናት ውስጥ（የጥገኝነት እውቅና አልተፈቀደልዎትም የሚል ውሳኔ （ተቀባይነት ያለመገኘት ውሳኔ) ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ ሳይሆን ውሳኔው ከተነገረዎት ቀን ጀምሮ ነው የሚቆጠረው） ማስገባት አለብዎ። የይግባኝ ማመልከቻ ፎርም አብዛኛውን ጊዜ የጥገኝነት እውቅና አላገኙም የሚል ውሳኔ በተነገረበት ወቅት ይሰጥዎታል ግን ካልተሰጠዎ በኢምግሬሽን ቢሮ እንዲሰጥዎ ይጠይቁ። ከዚያ በኋላ ይግባኝ ካመለከቱበት ቀን ጀምሮ በ6 ሳምንት ውስጥ statement ወረቀት ያስገባሉ（እስከተወሰነበት ቀን ገደብ ድረስ ማስገባት የማይችሉ ከሆነ የቀን ቀደብ በተመለከተ ኢሚግሬሽንን ያማክሩት）።

### ④ ይግባኝ ፕሮሴስ በተመለከተ የሚካሄድ ንግግርና ቃለ መጠይቅ እና ውሳኔው

በይግባኝ ፕሮሴስ ንግግርንና ቃለ መጠይቅን መጠየቅ ይችላሉ። በንግግርና ቃለ መጠይቅ ላይ የሬፉጂ አማካሪዎችም የሚገኙ ሲሆን ሌላው ደግሞ <u>ተወካይ ወይም ጠበቃ መገኘትም ይቻላል</u>። አብዛኛውን ጊዜ 1 ጊዜ ሲሆን ለመተርጉም ከሚያስፈልግ ሰዓትና ካማካሪዎች ጋር ከሚደረግ ጥያቄና መልስ ጋር ለ2 ሰዓት ያህል ይሆናል። ሲካሄድ በረዳትነቱ ወይም በታዛቢነቱ ጓደኛዎ ወይም ከእርስዎ ግንኙነት ያለው ሰው በቃለ መጠይቅ ተገኝቶ ሀሳብ መናገር ሊፈቀድም ይችላል። እንደሱ ከሆነ ለኢሚግሬሽን ደብዳቤ አስገብተው ማን እንደሚሳተፍ ማሳወቅ አለብዎ።

ከንግግርና ቃለ መጠይቅ በኋላ የይግባኝ ውሳኔ ይነገርዎታል። ተቀባይነት ያለመገኘት ውሳኔ ስህተት ነው ከተባለ የጥገኝነት እውቅና ይሰጥዎታል ግን ተቀባይነት ያለመገኘት ውሳኔ ትክክል ነው (ለይግባኝ ምክንያት የለውም) ከተባለ የጥተኝነት እውቅና ጥያቄ ፕሮሰስ ያልቅና ለሁለተኛ ይግባኝ ለመጠየቅ አይቻልም። በተረፈ አዲስ ምክንያት የተፈጠረ ከሆነ እንደገና የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ መጠየቅ የተከለከለ አይደለም።

### ⑤ አስተዳደራዊ ክስ(የፍርድ ቤት ምርመራ)

ለይግባኝ ምክንያት የለውም ከተባለ የፍርድ ቤት ምርመራ ለመጠየቅ ይችላሉ። የሚጠይቁ ከሆነ የይግባኝ ውሳኔ ካወቁበት ቀን ማግስት ጀምሮ 6 ወር ውስጥ (ለምሳሌ በ1ኛ ወር 10 ቀን ያወቁ ከሆነ እስከ 7ኛ ወር 10 ቀን ድረስ ነው። ነገር ግን የመጨረሻ ቀን የዕረፍት ቀን ከሆነ እስከሚቀጥለው ቀን ድረስ ነው) ክስ መመስረት አለብዎ። የክስ ፕሮሴስ ደግሞ በመጀመሪያ የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ተቀባይነት ያለመገኘት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በይግባኝ ፕሮሴስ ላይ እያለ ማድረግም ይቻላል።

በተረፈ ተቀባይነት ያለመገኘት ውሳኔ እንዲሰረዝ በመጠየቅ ክስ የሚመሰርቱ ከሆነ ለፍርድ ቤት አብዛኛውን ጊዜ የ8200 ዬን ስታምፕና 6400 ዬን ያህል የሚሆን የፖስታ ቴምብር አስቀድሞ እንዲያስገቡ ይጠየቃሉ። ሌለው ደግሞ ከዚህ ውጭ በችሎት አስተርጓሚ የሚያስፈልግ ከሆነ የተወሰነ ሺህ ዬን የሚሆን ለአስተርጓሚ የሚውል ክፍያ አስቀድሞ እንዲከፍሉ ይጠየቃሉ። እነዚህን ለክስ የሚያስፈልግ ወጭ ለመሸፈን አቅም ከሌለዎ ክስ ሲመሰረት በፍርድ ቤት የክስ እርዳታ ጥያቄም አንድ ላይ ያመለክታሉ።

## 2. የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ መሰረታዊ ነገሮች

ከዚህ በታች የተጻፈው ነገር የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ለማመልከት ሲያዘጋጁ የሚጠቅምዎ ኢንፎርሜሽን ይመስለናል።

### 1) ስቃይ ማለት ምንድን ነው?

የUNHCR (የተባበሩት መንግሥታት ሬፉጂ ከፍተኛ ኮሚሽነር ቢሮ) የሬፉጂ እውቅና መመዘኛ መጽሐፍ እንደሚገልጽ ማንኛውም የሚቀበል የ "ስቃይ" ፍቺ የለም። የሬፉጂ ስምምነት አንቀጽ 33 ስንመለከት "ስቃይ" ማለት ሕይወትን ወይም ነጻነትን የሚመለከት ፍርሃት ነው ብለን መገመት እንችላለን። ሌላው ደግሞ ከፍተኛ የሆነ የሰብአዊ መብት ረገጣም ከስቃዮች አንዱ ነው ብለን ማሰብ እንችላለን።

በተጨማሪ ደግሞ እሱ ራሱ ስቃይ ነው ለማለት ከማያስችል ነገር (ለምሳሌ የተለያየ መለየት) ወይም ሌላ ከሚጐዳዎ ምክንያት (ለምሳሌ ያገርዎ ባጠቃላይ ያልተረጋጋ ሁኔታ) ጋር የተያያዘ እርምጃ ተጠቂ ሊሆኑም ይችላሉ። እንደሱ ከሆነ የሚመለከትን ምክንያትም አንድ ላይ ግምት ውስጥ የምናስገባ ከሆነ ልብዎ ውስጥ በ "ተከመሩት ምክንያቶች" የተነሣ ስቃይ ሊደርስብኝ ይችላል የሚል በቂ ምክንያት ያለው ፍርሃት እንዳለዎ ማሳመንም ሊቻል ይችላል። የተከመሩት ምክንያቶች የሚለው ምን ዓይነት ነገር ከሆነ ሬፉጂ እንደሆነ ማሳመን እንደሚችል አጠቃላይ መርህን በግልጽ መግለጽ አይቻልም። በእርግጥ የግል ጂኦግራፊያዊ የሆኑ፤ ታሪካዊ የሆኑ እና ዘርን የተመለከቱ ነገሮችንም ጨምሮ በሁኔታዎች ሁሉ ይወሰናል።

ለምሳሌ ስቃይ ማለት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው።

**ሕይወትዎንና የሰውነት ደህንነትዎን እና ነጻነትዎን የሚመለከት ፍርሃት**

- የሕይወት አደጋ; ባገርዎ ውስጥ የመንግስት ጥቃት አላማ ሲሆኑ ወዘተ።
- እስራት; ፕሮሴሱ ሕጋዊ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል። ያሰረው ፖሊስ ቢሆንም ደህንነት ቢሆንም የደፈጣ ተዋጊ ቢሆንም መንግስት ዜጎችን የመጠበቅ ፍላጐት ወይም ብቃት እንደሌለው ማስረዳት የሚቻል ከሆነ "ስቃይ" ነው ለማለት ይቻላል። በውነት የታሰሩበት ኬዝ ብቻ ሳይሆን ሊታሰሩ ሲሆን የሸሹበት ኬዝም አንድ ነው።
- ቶርች: ባጠቃላይ "ቶርች" ነው ተብሎ ከሚታይ ሁኔታ ውጭም ብዙ ዓይነት አለ። ለምሳሌ በታሰሩበት ወቅት ምግብ ወይም የሚተኙበት ሰዓት አለመስጠትም ቶርች ነው።
- ዛቻ: ራስዎ ወይም ቤተሰቦችዎ ወይም ጓደኞችዎ ቀጥታ ሲዛቱ ወዘተ።
- መጥፋት: ራስዎ ወይም ቤተሰቦችዎ ወይም ጓደኞችዎ ታፍነው ሲጠፉ ወዘተ።

የምጣኔ ሃብታዊ ኑሮና የንብረት ደህንነትና ነጻነት በተመለከተ

- የንብረት እገዳ
- ሥራ መከልከል፤ የመሥራት እድል መከልከል
- የትምህርት እድል መከልከል

ሌሎች

- አስገድዶ ሃይማኖትን ማስቀየር ወይም ማሳመን
- የፖለቲካ ፓርቲ አባል እንዲሆን ወይም የፖለቲካ ፓርቲ አባልነት እንዲያቁም ማስገደድ

2) ሬፉጂ ነው ለማለት የሚያስችል የስቃይ ምክንያት

- ዘር：ብሔርንና ጐሳንም ጨምሮ
- ሃይማኖት
- ዜግነት
- የፖለቲካ አመለካከት; ማንኛውንም የፖለቲካ ንግግርና የፖለቲካ እንቅስቃሴ ያካትታል።
- የሆነ ማህበራዊ ቡድን አባል; አብዛኛውን ጊዜ ተመሳሳይ የሆነ ታሪክ፤ ወግ፤ ማህበራዊ ሁኔታ ካላቸው ሰዎች የሚመሰረት ቡድን ሲሆን የሆነ ማህበራዊ ቡድን አባል በመሆን ብቻ ከሆነ ሬፉጂ መሆንን ለማስረዳት በቂ አይደለም ይባላል። ነገር ግን እንደሁኔታው አባልነት ራሱ ስቃይ የመድረስ ፍርሃት አለ ለማለት የሚያስችል በቂ ምክንያት ሊሆንም ይችላል።

3) ስቃይ ማስረዳት

የሬፉጂ እውቅና መመዘኛ መጽሐፍ እንደሚገልጽ የማስረዳት ኃላፊነት አለዎ። ማለትም ከዚህ በታች የተጻፉት ነገሮችን ማድረግ አለብዎ።

1）እውነትን ለማስረዳት እውነትን መናገር እና መርማሪን በደንብ መርዳት

2）ማግኘት በሚቻል ማስረጃ የተናገሩትን ቃል ለመደገፍ እና ማስረጃ ከሌለ አሳማኝ የሆነ መግለጫ ለመስጠት ጥረት ማድረግ። አስፈላጊ ከሆነ የተጨማሪ ማስረጃ ለማግኘት ጥረት ማድረግ።

3）መርማሪ የሚመለከቱ ነገሮችን ለማረጋገጥ የሚያስችል መጠን የሆነ ዝርዝር የሆነ የደረሰብዎን ነገር የሚመለከት ኢንፎርሜሽን ማስጠት። ለተናገሩት ዝርዝር ሁሉ የተጣራ መግለጫ መስጠት።

ባዳጋ ውስጥ ያሉበትን ምክንያት ለጃፓን መንግስት በዝርዝር መግለጽ ነው በጣም ወሳኝ የሆነው። የዜግነትዎ  አገር (ወይም የሚኖሩባት አገር) መንግስት ሰብዓዊ መብት ይጥሳል ወይም ባጠቃላይ ሁኔታው ያልተረጋጋ ነው ማለት ብቻ ከሆነ በቂ ምክንያት አይሆንም። በእርስዎ ላይ ስቃይ የሚደርስበትን ተጨባጭነት ያለውን ምክንያት ማስረዳት ያስፈልጋል። በተረፈ ኢምግሬሽን የሚገቡ ዶክሜንቶችን ፎቶኮፒ አንስተው ቢያስቀምጡ ጥሩ ነው።

## 3. የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ለማመልከት የሚዘጋጁ ዶክሜንቶች

ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ዶክሜንቶች ያዘጋጁ። ሁሉንም ፎቶ ኮፒ አንስተው ቢያስቀምጡ ጥሩ ነው።

- አንድ የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ማመልከቻ ፎርም（ሳይዙ A4 ሆኖ 12 ገጽ ያለው）

- አንድ የግል መግለጫ (statement) ወረቀት（አስፈላጊ ባይሆንም ለጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ምርመራ ወሳኝ ነው። በማንኛውም ወረቀት ላይ መጻፍ ይቻላል）
- ሌላ ሬፉጂ መሆንዎን የሚገልጽ ማስረጃ
- ሁለት የእርስዎ ፎቶግራፍ（5 cm ×5 cm、ኮፍያ ሳያደርጉ ከፊትዎ በ2 ወር ውስጥ የተነሳ）(የመኖሪያ ፈቃድ ከሌለዎ 3 ፎቶግራፍ）

ሲያመለክቱ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ዶክሜንቶች ማሳየት አለብዎ።

- ፓስፖርት፤ የጉዞ ምስክር ወረቀት (travel document) ወይም መኖሪያ ፈቃድ（ካለዎ）
- አልያን ካርድ (resident card)（ካለዎ）
- ጊዜያዊ መልቀቂያ (certificate of provisional release, kari houmen)（ካለዎ）
- የመግቢያ ፈቃድ ለምሳሌ መግቢያ ፈቃድ ለጊዜያዊ ጥበቃ ወዘተ（ካለዎ）

### 1） የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ማመልከቻ ፎርም ማግኘት

ከካናጋዋ ኬን ውጭ የሆነ ካንቶ ኮሺንኤትሱ ሰፈር（ቶክዮ ቶ፤ ሳይታማ ኬን፤ ቺባ ኬን፤ ቶቺጊ ኬን፤ ጉማ ኬን፤ ኢባራኪ ኬን፤ ያማናሺ ኬን፤ ናጋኖ ኬን፤ ኒጋታ ኬን）ነዋሪ ከሆኑ የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ማመልከቻ ፎርምን በሺናጋዋ（ቴኖዙ አይል）በሚገኝ ቶክዮ ኢሚግሬሽን 3ኛ ፎቅ በሬፉጂ ምርመራ ክፍል ለማግኘት ይችላሉ። እዚያ ሄደው የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ለማመልከት እንደሚፈልጉ ይንገሩዋቸው። የካናጋዋ ኬን ነዋሪ ከሆኑ በቶክዮ ኢሚግሬሽን ዮኮሃማ ቅርንጫፍ ለማግኘት ይችላሉ።

ሌላው ደግሞ በፍትፍ ሚኒስቴር ድህረ ገጽም ማመልከቻ ፎርምን（የPDF ፋይል）ለማግኘት ይችላሉ（http://www.moj.go.jp）። ማመልከቻ ፎርም ደግሞ በተለያየ ቋንቋ ተዘጋጅቷል（እንግሊዝኛ፤ አማርኛ፤ አረብኛ፤ ኢንድነዝያኛ፤ ሺንሃልኛ፤ እስፓንኛ፤ ሱዋሂልኛ፤ ታይኛ፤ ታጋሎግኛ፤ ታሚልኛ፤ ዳርኛ፤ ቱርክኛ፤ ኔፓልኛ፤ ፓሽቱኛ፤ ፓንጃብኛ፤ ህንድኛ፤ ፈረንሳይኛ፤ ቬትናምኛ፤ ፋርስኛ፤ ቤንጋልኛ፤ ፖርቱጋልኛ፤ ምያማርኛ፤ ሞንጎልኛ፤ሩሲያኛ፤ ኡርዱኛ)። በJAR ም ማመልከቻ ፎርም ማግኘት ይችላሉ።

※"ከካናጋዋ ኬን ውጭ የሆነ ካንቶ ኮሺንኤትሱ" ውጭ ከሆነ በተጨማሪ Ⅱ በየሰፈሩ ኢሚግሬሽን የት እንዳለ ያረጋግጡ። **በተረፈ በኢሚግሬሽን እስር ቤት ወዘተ ታስረው የሚገኙ ከሆነ የእስር ቤቱን ወዘተ ሠራተኛ አናግረው ማመልከቻ ፎርምን ያግኙ። በኤር ፖርት ውስጥ ስለጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ኢንፎርሜሽን የሚፈልጉ ከሆነ የኢሚግሬሽን ሠራተኞችን ይጠይቁዋቸው። ወይም JARን (ስልክ 0120-477-472/03-5379-6003) ወይም UNHCRን (ስልክ 03-3499-2011) መጠየቅም ይችላሉ።**

### 2） የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ማመልከቻ ፎርም መሞላት

ማመልከቻ ፎርም ደግሞ ራስዎ መሞላት አለብዎ። በአፍ መፍቻ ቋንቋ ወዘተ ከሁሉም በሚችሉበት ቋንቋ ስህተት እንዳይኖር በማድረግ ይጻፉ። ለምሳሌ ማንበብ ማጻፍ ባለመቻልዎ ምክንያት መሞላት የማይችሉ ከሆነ የኢምግሬሽን ሠራተኞችን ያማክሩዋቸው። ማመልከቻ ፎርምን ሲሞሉ ወሰን ባለ ትንሽ በሆነ ቦታ ላይ ሁሉንም መጻፍ አያስፈልግም። እንደቦታው "በመግለጫ (statement) ላይ እንደተጻፈ" ወይም "መግለጫዬን ይመልከቱ" የሚለውን ብቻ ጽፈው ዝርዝርን የጻፉበት መግለጫ ወረቀትን ማያያዝም ይችላሉ።

### 3） የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ማመልከቻ ፎርም የሚገባበት ቦታ

ለኢምግሬሽን ሬፉጂ መርማሪ ነው የማመልከቻ ፎርምን የሚሰጡት። ማመልከቻ ፎርሙን ሲቀበሉ "ደረሰኝ" ይሰጥዎታል። ደረሰኙ ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ በፓስፖርት ላይ ይያያዛል። በደረሰኙ ላይ የምዝገባ ቁጥር አለ። ደረሰኙን መቀበል በጣም ወሳኝ ነው። ኢሚግሬሽን ማመልከቻ ፎርምን ቢቀበልም ደረሰኝ ካልተሰጠዎ ትክክለኛ ተቀባይነት የለውም ሊባልም ይችላል። ሌላው ደግሞ ይህ ደረሰኙ የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ፕሮሴስ እስከሚያልቅ ድረስ እንዳይጠፋብዎ ይያዙት።

## 4） የግል መግለጫ (Personal Statement) መጻፍ

የግል መግለጫ ወሳኝ ከሆኑ ዶክሜንቶች አንዱ ነው። ስለዝርዝሩ ደግሞ **"Self Help Kit"** የሚልን ሌላ ወረቀት ይመልከቱ። በመግለጫ ወረቀት ላይ ወዳገርዎ መመለስ የማያስችልን ሁኔታ በዝርዝር ይገልጻሉ። በግል መግለጫ ላይ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ነገሮች ይገልጻሉ።

1. የስቃይ ሁኔታ － ምን ዓይነት የሆነ ስቃይ እንደነበረ፤ ምን ዓይነት ነገር እንዳጋጠመዎ።
2. የስቃይ ምክንያት － በእርስዎ ላይ ለምን ስቃይ እንደደረሰብዎ ወይም ስቃይ ሊደርስብዎ እንደሚችል።
3. ባሁኑ ሰዓት ያለ ሁኔታ － ወዳገርዎ የሚመለሱ ከሆነ ስቃይ ሊደርስብዎ እንደሚችል።
4. ከላይ በተራ ቁጥር １～３ ላይ ስለተጻፈው ዝርዝር የሆነ መግለጫ － በእርስዎ ላይ የደረሰብዎ ነገር ብቻ ሳይሆን ስለቤተሰቦችዎ፤ ስለጓደኞችዎና አበል ስለሆኑበት ድርጅትም ምሳሌ ጠቅሰው መግለጽ አለብዎ።

በግል መግለጫ ላይ በተቻለ መጠን በዝርዝር ሁኔታውን ይጻፉ። ከተወለዱበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ የነበረውን ሁኔታ（አስፈላጊ ከሆነ ስለቤተሰቦችዎና ስለዘመዶችዎም）መጻፍ አለብዎ። ነገር ግን ከሁሉም ወሳኝ የሆነው በእውነት የደረሰብዎ（ወይም ሊደርስብዎ የነበረ）ስቃይ የሚመለከት መግለጫ ነው። ስም፤ ቀን፤ ቦታ፤ ምን ከተፈጠረ በኋላ ምን እንደተፈጠረ ወዘተ ማለትም ተጨባጭነት ያለው መግለጫ ወሳኝ ነው። በእርስዎ ራስዎ ላይ የደረሰብዎን ነገርና በእውነት ባደገኛ ሁኔታ የተጋለጡበትን ምክንያት ተጨባጭነት ባለው መልክ ይጻፉ።

በግል መግለጫ ወረቀት ላይ "5W1H"（መቼ፤ የት፤ ማን፤ ምንን፤ በማን ላይ፤ እንዴት）የሚለውን ተጠንቅቀው በእርስዎ ላይ（ወይም በቅርብ ዘመድዎ ወዘተ ላይ）የደረሰብዎን ነገር ሌላው ደግሞ ባገርዎ የሚቆዩ ከሆነ ወይም ወደፊት የሚሄዱ ከሆነ የሚደርስብዎን ነገር ይጻፉ። ከማመልከቻ ፎርም ጋር አያይዘው ስለሚያስገቡ ማስረጃም ይግለጹ። ያጠቃላይ ሁኔታ ብቻ ሳይሆን በራስዎ ላይ በደረሰብዎ ነገር（ከቅርብ ዘመድዎ ወዘተ የሰሙትን ነገርም ጨምሮ）ላይ ትኩረት ሰጥተው ይጻፉ።

ዝርዝርን ለመጻፍ ስለሚያስፈልግ አብዛኛውን ጊዜ የግል መግለጫ ወረቀት ረጅም ይሆናል። ከሁሉም ወሳኝ የሆነው ለራስዎ ጥበቃ የሚያስፈልግበትን ተጨባጭነት ያለውን ምክንያትን መግለጽ ነው። የግል መግለጫ ወረቀትን ፎቶ ኮፒ ማንሳትን እንዳይረሱ። የግል መግለጫ ደግሞ ለጥገኝነት እውቅና ጥያቄ መሰረታዊ የሆነ ወሳኝ የሆነ ዶክሜንት ነው። በቃለ መጠይቅ ጊዜ ከግል መግለጫው የሚጋጭ ነገር ቢናገሩ ሊጐዳዎትም ይችላል።

## 5） ሌሎች ማስረጃዎች

የጥገኝነት እውቅና ለማግኘት የሚናገሩትን ማስረዳት አለብዎ። ለዚህም ወደአገርዎ የሚመለሱ ከሆነ ስቃይ ሊደርስብዎ እንደሚችል የሚገልጽ ማስረጃ ያግኑ። በርግጥ ማስረጃ ማግኘት ሳይከብድ አይቀርም። ነገር ግን የሚናገሩትን ለማስረዳት በተቻለ መጠን ብዙ ዶክሜንት ማዘጋጀት ወሳኝ ነው። የሬፉጂ መርማሪ ማስረጃ እንዲያስገቡ ባይጠይቅም ራስዎ በተቻለ መጠን ማስራጃዎችን ሰብስበው ያስገቡ።

ለምሳሌ ከዚህ በታች የተጠቀሱት ነገሮች የሚጠቅም ማስረጃ ይሆናል።

●የእርስዎ እንቅስቃሴ ወይም በእውነት የደረሰብዎ ስቃይ የሚገልጽ የጋዜጣ ወይም የመጽሔት ጽሁፍ ወዘተ

●የእርስዎ የፖለቲካ አመለካከት የሚያሳውቅ ጽሁፍ ወዘተ

●እርስዎን በተመለከተ ያገርዎ መንግስት ያወጣ የማፈላለግ ወይም የማሳሰር ማዘዣ ወዘተ ማለትም የማሰቃየት ፍላጐት የተገለጸበት ዶክሜንት

●አባል የሆኑበት ድርጅት ያባልነት መታወቂያ（እርስዎ አባል መሆኑን ወይም አባል በሆኑበት ድርጅት ውስጥ ያለዎን ስልጣን

ወይም የሚያደርጉን እንቅስቃሴ የሚገልጽ ወረቀት ወዘተ)

●እርስዎ ከሚናገሩ ቃል ጋር የሚያያዝ መታወቂያ፤ የተማሪነት መታወቂያ ወዘተ

●የውጭ አገር መንግስት አካል ወይም ሰብዓዊ ሙብት ተሟጋች ያወጣ ሪፖርት ወዘተ። ለምሳሌ ያሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፤ የእንግሊዝ ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር፤ የአምኔስቲ ኢንተርናሽናል (Amnesty International)፤ የህዩማን ራይትስ ዎች (Human Rights Watch) ሪፖርት ወዘተ

ዶክሜንቶች ሁሉ ስለእርስዎ በዝርዝር የሚገልጽ መሆን አያስፈልግም። ለምሳሌ አባል የሆኑበት ድርጅት በጻፈ ምስክር ወረቀት ላይ ስምዎና በድርጅት ውስጥ ያለዎ ስልጣን ወዘተ በግልጽ ተጽፎ ባገርዎ ውስጥ የደረሰብዎ ነገርም የሚጻፍ ከሆነ በጣም ጥሩ ነው እንጂ በተራ ጋዜጣ ጽሁፍ ከሆነ ስለእርስዎ የሚገልጽ ባይሆንም ችግር የለም። በድርጅትዎ አባላት ላይ ስቃይ ደርሶባቸዋል የሚል ጽሁፍ ቢሆንም በቂ ነው። የሰብዓዊ ሙብት ተሟጋቾች ሪፖርትም እንደሱ ነው። ስምዎ በሪፖርት ላይ ባይገኝም ትልቅ ዶክሜንት ይሆናል። እንደእርስዎ በሆኑ ሰዎች ላይ ስቃይ ደረሰባቸው የሚል ሪፖርት ከሆነ ለማስገባት በቂ ዋጋ ያለው ዶክሜንት ይሆናል።

ወሳኝ የሆነ ዶክሜንት ኦሪጅናል በእጅዎ ላይ ይቀመጥና ፎቶ ኮፒውን ለሬፉጂ መርማሪ እንዲሰጡ። የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ሲያመለክቱ ወይም ቃለ መጠይቅ ሲደረግ ለሬፉጂ መርማሪ ኦሪጅናልን አሳይተው ፎቶ ኮፒውና ኦሪጅናሉ አንድ መሆንን ያረጋግጥ። የዶክሜንት ኦሪጅናል አያስገቡ።

## 4. ጊዜያዊ ቆይታ (Provisional Stay, Karitaizai)

የመኖሪያ ፈቃድ ሳይኖርዎ የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ሲያመለክቱ የተወሰኑ ቅድመ ሁኔታዎች የሚሟሉ ከሆነ ጊዜያዊ ቆይታ ይ ፈቀድልዎታል። የጊዜያዊ ቆይታ ፈቃድ ለማግኘት ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት አለብዎ።

(1)ከጃፓን አገር የማስወጣት ፕሮሴስ የሚያስፈጽም ልዩ ምክንያት አለ ብሎ ለመጠርጠር በቂ ምክንያት አለመኖር
(2)ጃፓን ከገቡበት ቀን (በጃፓን እያሉ ሬፉጂ የሆኑበት ምክንያት የተፈጠረ ከሆነ እሱን ካወቁበት ቀን) ጀምሮ 6ወር ውስ ጥ የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ማመልከት
(3)ስቃይ የመድረስ ፍርሃት እንዳለ ከሚታወቅበት ቦታ ቀጥታ ወደጃፓን ሲገቡ
(4)ጃፓን ከገቡ በኋላ የወንጀል ሕግን ወይም ሌላ ሕግን ተላልፈው በቅጣትነት ያልታሰረ መሆን
(5)ገና ከጃፓን አገር የማስወጣት ማዘዣ ወረቀት አለመውጣት
(6)ይጠፋል ለማለት የሚያስችል በቂ ምክንያት አለመኖር

"ቀጥታ ወደጃፓን ሲገቡ" የሚለውን በተመለከተ፤ ጥበቃ የሚፈልጉ አብዛኞች ካገር ቤታቸው ወደጃፓን "ቀጥታ" መምጣት ስ ለሚከብዳቸው በጥብቅ ላይፈታም ይችላል። ወደጃፓን ለምን "ቀጥታ" መግባት እንዳልቻሉ ምክንያቱን በዝርዝር መግለጽ ይች ላሉ። ጊዜያዊ ቆይታ አብዛኛውን ጊዜ ለ6 ወር ነው። ቆይታው ለማለቅ ከ10 ቀን በፊት ጀምሮ የጊዜያዊ ቆይታ እድሳትን ለማ መልከት ይችላሉ። ይህ ጊዜያዊ ቆይታ በተፈቀደበት ጊዜ ውስጥ አይታሰሩም። ከጃፓን አገር የማስወጣት ፕሮሴስም ይቆማል።

ጊዜያዊ ቆይታ የሚፈቀድልዎ ከሆነ የጊዜያዊ ቆይታ ፈቃድ እስከሚነሳ ድረስ ከጃፓን አገር የማስወጣት ፕሮሴስ ይቆማል እንጂ ጊዜያዊ ቆይታ ካልተፈቀደልዎ ከጃፓን አገር የማስወጣት ፕሮሴስ ሳይቆም የማስወጣት ማዘዣ ወረቀት ሊወጣም ይችላል። ነገ ር ግን የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ እስካመለከቱ ድረስ አስገድዶ አያስወጡዎትም።

## 5. በሰብአዊ ርህራሄ ምክንያት የሚሰጥ ልዩ መኖሪያ ፈቃድ

የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ተቀባይነት ባያገኝም በሰብአዊ ርህራሄ ምክንያት መኖሪያ ፈቃድ ሊሰጥዎም ይችላል። መኖሪያ ፈቃድ እያለዎ የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ያመለከቱ ከሆነ መኖሪያ ፈቃድዎ ይቀየራል ወይም ይራዘማል። መኖሪያ ፈቃድ ከሌለዎ ልዩ

መኖሪያ ፈቃድ[1] ይሰጥዎታል። የኢሚግሬሽን ቁጥጥር እና ሬፉጂ እውቅና ሕግ እንደሚለው በጃፓን ቆይታን የሚያስፈቅድበት ልዩ ምክንያት ካለ ቆይታ ይፈቀድልዎታል። ሌላ በኩል ደግሞ "ልዩ ምክንያት" የሚልን ለመወሰን ግልጽ የሆነ መመዘኛ ይፋ አልተደረገም። የፍትህ ሚኒስቴር ባጠቃላይ የእርስዎ ⅰ)በፊት የተመዘገበ መረጃ፤ ⅱ)ቤተሰቦች አባላት፤ ⅲ)ያገሪት ሁኔታ ወዘተ የሚልን ነገር ግምት ውስጥ ያስገባል ተብሎ ይገመታል። የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ካመለከቱ ከጃፓን አገር የማስወጣት ፕሮሴስ ውስጥ ሳይሆን በጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ፕሮሴስ ውስጥ ልዩ መኖሪያ ፈቃድ አስፈላጊ ይሁን አይሁን እንደሚታይ ይወቁ።

## 6. ከጃፓን አገር የማስወጣት ፕሮሴስ (Deportation, Taikyo Kyosei Tetsuzuki)

መኖሪያ ፈቃድ ሳይኖርዎ የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ የሚያመለከቱ ከሆነ የኢሚግሬሽን የትልልፍ ምርምር ክፍል እንዲቀርቡ ደብዳቤ ሊልክልዎ ወይም ስልክ ሊደውልልዎ ይችላል። ይህ እንዲቀርቡ የሚል ጥያቄ የሬፉጂ እውቅና የሚመለከተው ሳይሆን ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ የሚቆዩበት ወይም የገቡበት ምክንያትን ለማጣራት የሚደረግ ሲሆን ከጃፓን አገር የማስወጣት ፕሮሴስ አንዱ ነው። ከጃፓን አገር የማስወጣት ፕሮሴስ አብዛኛውን ጊዜ ከዚህ በታች እንደሚታይ ተራ በተራ ይካሄዳል (የኢሚግሬሽን ሕግ ካንቀጽ 27 እስከ 55 ይመልከቱ)።




### 1) የትልልፍ ምርምርና ምርመራ

በመጀመሪያ (በቶኪዮ ኢሚግሬሽን ከሆነ በ6ኛ ፎቅ ላይ በምርመራ 3ኛ ክፍል እና በትልልፍ ምርምር ክፍል) የትልልፍ ምርምርና ምርመራ ቃለ መጠይቅ ይደረጋል። በዚህ ወቅት ለኢሚግሬሽን ቁጥጥር ጠባቂና መርማሪ ወዳገርዎ መመለስ የማይችሉበትን ምክንያት ይናገሩ።

---

[1] ልዩ መኖሪያ ፈቃድ ማለት መኖሪያ ፈቃድ ለሌለው ውጭ ዜጋ የፍትህ ሚኒስትር ልዩ ምክንያት እንዳለ አምኖ ቆይታን የመፍቀድ ስርዓት ሲሆን ባዲሱ የቆይታ ፈቃድ ይሰጥዎታል።

2） ጊዜያዊ መልቀቂያ ማመልከት እና ጊዜያዊ መልቀቅ (Kari Homen)

የኢሚግሬሽን ሕግን ሲተላለፉ ከተገኙ አብዛኛውን ጊዜ ይታሰራሉ። ጊዜያዊ መልቀቂያ ማለት ባለመታሰር（በመፈታት）ፈንታ የተለያየ ግዴታ የመጠየቅ ስርዓት ሲሆን በቅጣት ፕሮሴስ ላይ ከሚደረግ በዋስ ከመፍታት ተመሳሳይ የሆነ ስርዓት ነው። ጊዜያዊ መልቀቂያ ከተፈቀደልዎ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን መጠበቅ አለብዎ።

- ●ከ፣ እስከ 3 ወር ውስጥ አንዴ ወደኢሚግሬሽን መቅረብ
- ●ከሚኖሩበት ክልል (ቶዶፉኬን) አለመውጣት （ነገር ግን ካመለከቱ የጉዞ ወዘተ ፈቃድ ማግኘት ይችላሉ）
- ●አድራሻ የሚቀይሩ ከሆነ ማሳወቅ（አስቀድሞ እንዲያሳውቁ ይላል እንጂ ማሳወቅ ያለበት ወቅት በጥብቅ የተወሰነው አይደለም። ነገር ግን በእውነት ባሳወቁበት አድራሻ እንደሚኖሩ በሚገልጽ ማስረጃነት የቤት ኪራይ ውል ወረቀት ወዘተ ቼክ ሊደረግም ይችላል）።

ሌላው ደግሞ እነዚህን ግዴታዎች የሚያስከብር ዋስ እንዲሆን የዋስ ገንዘብ እንዲከፍሉ እና ዋስ የሚሆንልዎትን ሰው እንዲመርጡ ይጠየቃሉ። የዋስ ገንዘብ ካልጠፉ በስተቀር ፕሮሴስ ካለቀ በኋላ（ለምሳሌ ወዳገርዎ እንዲመለሱ ሲታሰሩ ወይም መኖሪያ ፈቃድ ካገኙ በኋላ）ይመለሳል። ዋስ ለሆነ ሰው የሚከብድ ግዴታ（ካሳ የመክፈል ኃላፊነት ወዘተ）ባይኖረውም ግዴታዎቹን እንደሚያስከብርዎ እንዲምል ይጠየቃል።

ጊዜያዊ መልቀቂያ ሲያመለክቱ የዋስ ገንዘብ እንዲከፍሉ ይታዘዛሉ። የዋስ ገንዘብ ቢበዛም 3 ሚሊዮን ዬን ሲሆን በእውነት የሚከፈል ዋጋ እንደሁኔታው ሆኖ ብዙ ልዩነት ስላለ ባጠቃላይ ስንት ነው በማለት መገመት አይቻልም（ብዙ የሆነ ዋስ ገንዘብ መክፈል የማይችሉ ከሆነ እንዲቀንስልዎ ከኢሚግሬሽን ጠባቂ ጋር ይደራደሩ）።

የዋስ ገንዘብ ሲከፍሉ “የጊዜያዊ መልቀቂያ ፈቃድ” ይሰጥዎታል። ከዚያ በኋላ ፕሮሴስ ወደሚቀጥለው የትልልፍ ምርመራ ይሻገራል።

አንዴ ጊዜያዊ መልቀቂያ ከተፈቀደልዎ አብዛኛውን ጊዜ ፈቃዱ ከጃፓን አገር የማስወጣት ፕሮሴስ ሁሉም እስከሚያልቅ ድረስ ይቀጥላል። ሌላው ደግሞ የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ያመለከተ ግለ ሰብ ተጠርቶ ወይም በፈቃደኝነቱ ቀርቦ ከጃፓን አገር የማስወጣት ፕሮሴስ ቢጀመርም አብዛኛውን ጊዜ የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ፕሮሴስ ሁሉም（የይግባኝ ፕሮሴስንም ጨምሮ）እስከሚያልቅ ደረስ የማስወጣት ፖሮሴስ የመጨረሻ ውሳኔ ስለማይሰጥ ዞርዞሮ አብዛኛውን ጊዜ የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ፕሮሴስ ሁሉም እስከሚያልቅ ድረስ የጊዜያዊ መልቀቂያ ፈቃድም ይቀጥላል።

3） ከዚያ በኋላ የሚደረግ ፕሮሴስ

በኢሚግሬሽን ጠባቂና መርማሪ የሚካሄድ የትልልፍ ምርምርና ምርመራ ውሳኔ “ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ መቆየት” “ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ መግባት” ነው የሚል ከሆነ በልዩ መርማሪ የሚካሄድ ቃለ ምልልስ（ኢንተርቭዩ）መጠየቅ ይችላሉ። በዚህ ቃለ ምልልስ ላይ ጠበቃዎና ጓደኛዎ መታዘብ ይችላሉ። የቃለ ምልልሱ ውሳኔም አንድ ሆኖ ውሳኔውን የሚቃወሙ ከሆነ ፍትህ ሚኒስትርን（ለክልል ኢሚግሬሽን ሃላፊ ስልጣን ሊረከብም ይችላል）እንደገና እንዲመረምር መጠየቅ ይችላሉ። ነገር ግን የጥገኝነት እውቅና ጥያቄዎን የፍትህ ሚኒስቴር እየመረመረ ሳለ ከጃፓን አገር የማስወጣት እርምጃ አይወሰድም።

## Ⅲ ጥያቄና መልስ

የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ አመልካቾች ብዙን ጊዜ የሚጠይቁ ጥያቄዎች ከዚህ በታች ስላሉ ይመልከቱ።

**1)የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ካመለከትኩ በኋላ ለትልልፍ ምርምር እንድቀርብ ከተባልኩ እንዴት ባደርግ ይሻላል?**

ከጃፓን አገር የማስወጣት ፕሮሴስን የሚገልጽ ምዕራፍን ያንብቡ።

ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ የሚቆዩ ከሆነ ወይም የገቡ ከሆነ የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ማመልከቻ ፎርም ሲያስገቡ ወደትልልፍ ምርምር ክፍል እንዲቀርቡ ሊጠየቁም ይችላሉ። የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ማመልከቻ ከመቀበላቸው በፊት በመጀመሪያ በኢሚግሬሽን ጠባቂ የሚካሄድ የትልልፍ ምርምር እንዲደረግ የሚል መግለጫ ሊኖርም ይችላል። ነገር ግን የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ከማመልከት በፊት የማስወጣት ፕሮሴስ እንዳይጀመር ከትልልፍ ምርምር በፊት እዚያ ለማንኛውም ማመልከቻ እንዲቀበሉ ቢያደርጉ ይሻላል።

**2)ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ጃፓን የምቆይ (ኦቨር ስተይ) ወይም የገባሁት ብሆንም የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ማመልከት እችላለሁ?**

ይችላሉ። ባሁኑ ሰዓት በጃፓን የሚገኙ ከሆነ ማንኛውም የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ማመልከት ይችላል። የመኖሪያ ፈቃድ ያገልግሎት ጊዜ ያለቀ (የተፈቀደልዎ ጊዜ ያለቀ ወይም የእድሳት ጥያቄ ያልተፈቀደልዎ) ቢሆንም በውሸት ፓስፖርት ተጠቅመው ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ የገቡ ቢሆንም ማመልከት ይችላሉ። ባመለከቱበት ቦታም አይታሰሩም።

**3)ለማመልከት የሚያስፈልጉ ዶክሜንቶች ሁሉም አይደለም በእጄ ላይ ያሉት። ሁሉንም እስከማገኝ ድረስ ከማመልከት ብቆጠብ ይሻላል?**

የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ካመለከቱ በኋላ በተጨማሪ ማስረጃ ማስገባትም ስለሚችሉ በተቻለ መጠን ቶሎ ማመልከቻ ፎርም ቢያስገቡ ይሻላል ብለን እናስባለን።

**4)ዶክሜንቶችን ለማስተርጐም የማልችል ከሆነ ችግር አለ?**

የፍትህ ሚኒስቴርና ኢሚግሬሽን እንደሚል ከሆነ የግል መግለጫ ወረቀትና ሌሎች ዶክሜንቶች ለማስተርጐም አመልካች ነው ኃላፊነት የሚወስደው። የሚቻል ከሆነ ወደጃፓንኛ የተተረጐሙ ዶክሜንቶችን እንዲያስገቡ እናሳስባለን። ለማንኛውም መጀመሪያ አካባቢዎ ያሉትን ጓደኞችን ወደጃፓንኛ እንዲተረጉሙ ይጠይቁ። ነገር ግን ለማስተርጐም ብዙ ወጭ ስለሚያስፈልግ "ማስረጃዎችን ዶክሜንቶችን ሁሉንም ለማስተርጐም" ላይችሉም ይችላል። የገባ ዶክሜንት በእንግሊዝኛ ወይም በሌላ ቋንቋ የተጻፈ ቢሆንም ለምርመራ የሚያስፈልግ ከሆነ በኢሚግሬሽን በኩል የሚተረጐም ይመስለናል። ነገር ግን በጃፓንኛ ከልተጻፈ መቶ በመቶ ይነበባል ለማለት አይቻልም።

**5)ጠበቃ ያስፈልገኛል?**

ጠበቃ ባይኖርዎም የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ማመልከት ይችላሉ። ነገር ግን በፕሮሴስ ላይ በሕግ ዙሪያ የሚሰጥዎ ምክር ይጠቅምዎታል። ተከፍሎ ወይም በነጻ ለውጭ ዜጎችን የማማከር አገልግሎት የሚሰጥ ጠበቃዎች ማኅበርም ስላለ አካባቢዎ ያለውን የጠበቃዎች ማኅበርን ያማክሩ። ጠበቃ የሚቀጥሩ ከሆነ አብዛኛውን ጊዜ ከ200 ሽህ እስከ 500 ሽህ ዬን የሚሆን ክፍያ ያስፈልጋል (ከዚህ በተጨማሪ ለማስተርጐምና ለትራንስፖርት ወዘተ የሚፈጅ ወጭም ሊያስፈልግ ይችላል)። ለጠበቃ የሚከፍሉ ገንዘብ ማዘጋጀት የማይችሉ ከሆነ እርዳታ የሚሰጥ ስርዓትም ስላለ ጠበቃዎን ያማክሩ።

**6)የጃፓን NGO ወዘተ ምን ዓይነት እርዳታ ይሰጣል?**

የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ አመልካች ከሆኑ ጃፓን ከሚገኝ NGO ወይም ከመንግስት ጋር ከተያያዘ ድርጅት በሕግ ዙሪያ ወይም ማህበራዊ የሆነ ምክርና እርዳታ ማግኘት ይችላሉ። ለምሳሌ JAR የሚባለው ሥራ ለማከናወን ከUNHCR ጋር የተዋዋለ ድርጅት

ሲሆን በጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ፕሮሴስ፤ በኢሚግሬሽን ፕሮሴስና በሌሎች የሚመለከቱ ሕጎችና ደንቦች ዙሪያ ይመክራል። የJAR የማኅበራዊ አገልግሎት ሠራተኞች ደግሞ በጤና፤ በሥራና በመኖሪያ ወዘተ ዙሪያ ለሬፉጂዎች የየእለቱ ኑሮ ስለሚያስፈልግ ነገር ምክርና እርዳታ ይሰጣሉ። የተጨማሪ እርዳታ የሚያስፈልግ ከሆነ JAR ደግሞ ለጃፓን አለም አቀፍ ማኅበራዊ ሥራ ድርጅት（ISSJ）እና ለጃፓን ወንጌላዊ ሉተራን ቤተ ክርስቲያን አባላት ማህበር（JELA）ወዘተ ባለሙያ ለሆነ NGO ይልካል። የሬፉጂዎች እርዳታ ዋና ቢሮን（RHQ）የመንግስት ገንዘብ እርዳታ መጠየቅም ይችላሉ።

## 7）የተባበሩት መንግሥታት ሬፉጂ ከፍተኛ ኮሚሽነር ቢሮ（UNHCR）ምን ዓይነት እርዳታ ይሰጣል?

የUNHCR ቶክዮ ቢሮ በተለይ ከዚህ በታች ስለተጠቀሱት ነገሮች የጃፓን መንግሥት የሬፉጂ ስምምነት ያክብር አያክብር ሞኒተሪንግ ያደርጋል (ይቆጣጠራል)።

- ባለም አቀፍ ደረጃ ጥበቃ ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች የጥበቃ ፕሮሴስ አክሴስን (ለመቅረብ የሚያስችል መንገድ) እና ጥበቃን ይስጥ አይስጥ
- ጥበቃ ለሚፈልጉት የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ውሳኔ እስከሚወጣ ድረስ ተገቢ የሆነ ሁኔታ ለመቅረብ የሚያስችል ሁኔታ ያመቻች አያመቻች（የኢንፎርሜሽን አክሴስ፤ አለመታሰር፤ አስፈላጊ ከሆነ ጥበቃ ለሚፈልጉት እቃ መስጠት፤ የልጆች ትምህርት፤ መሰረታዊ የሆነ የህክምና አገልግሎት ወዘተ）

ለዚህም UNHCR የፍትህ ሚኒስቴር የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ፕሮሴስን ሞኒተሪንግ አድሮጎ ለፍትህ ሚኒስቴር ሬፉጂዎች ስለመጡባቸው አገሮች አዲስ የሆነ ኢንፎርሜሽን ይሰጣል። ሌላው ደግሞ UNHCR ካማካሪነቱ ሚናዎች አንዱን ለመፈጸም ለኢሚግሬሽንና ለፍርድ ቤት የጥገኝነት እውቅና ፍች በተመለከተ በሕግ ዙሪያ አስተያየት ያቀርባል።

UNHCR ደግሞ ጥበቃ ለሚፈልጉትና ለሬፉጂዎች እርዳታ ለመስጠት ከJAR ጋር ሥራ የማከናወን ውል ተዋውሏል። ከዚህ በታች የተጠቀሱት ነገሮች የሚፈልጉ ከሆነ ለማንኛውም JARን ያናግሩ።

- የጥገኝነት እውቅና ጥያቄን ፕሮሴስ የሚመለከት ምክር
- የጥገኝነት እውቅና ጥያቄን ካመለከቱ በኋላ የእቃ እርዳታን የሚመለከት ምክር
- የሕግ ፕሮሴስን የሚመለከት የጠበቃ እርዳታ
- የጊዜያዊ መልቀቂያ ፈቃድ ለማግኘት የሚያስፈልግ ምክር
- የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ካመለከቱ በኋላ የጃፓንን ኑሮ የሚመለከት ሌላ ኢንፎርሜሽን

## 8）የሬፉጂ መርማሪ ቃለ መጠይቅ ምን ዓይነት ነገር ነው?

በሬፉጂ መርማሪ በሚካሄድ ቃለ መጠይቅ ላይ አብዛኛውን ጊዜ ረጅም ሰዓት የሚፈጅ ቃለ መጠይቅ ለተወሰኑ ቀናት ሊካሄድም የሚችል ሆኖ ማመልከቻውን በተቻለ መጠን በትክክል ለመገንዘብ ብዙ ጥያቄ ይጠየቃል። እውነትን ለማረጋገጥና ስህተት እንዳይኖር በተደጋጋሚ ተመሳሳይ የሆነ ጥያቄ ሊደጋገምም ይችላል። ለጥያቄ እውነትን መልሰው አንድም ሳያስቀሩ ተጠንቅቀው በዝርዝር ሁኔታውን መግለጽ ነው ወሳኝ የሆነው።

በሬፉጂ መርማሪ የሚካሄድ ቃለ መጠይቅ ሲካሄድ ያፍ መፍቻ ቋንቋዎ የሚናገር አስተርጓሚ አለ። ለምሳሌ ባስተርጓሚው ችሎታ ወይም በፖለቲካ አቋም ወዘተ ላይ ጥርጣሬ ካለ አስተርጓሚ እንዲቀየር መርማሪውን ይጠይቁ። ችሎታ ያለውና አድላዊነት የሌለው አስተርጓሚ እንዲኖር አድርገው በመግባባት ላይ ስህተት እንዳይኖር ማድረግን እንዳይረሱ።

የሬፉጂ መርማሪ ደግሞ በቃለ መጠይቅ ሲደረግ በጃፓንኛ ማስታወሻ ይዞ ስቴትሜንት ወረቀት ከጻፈ በኋላ ባስተርጓሚ አማካይነት የተጻፈውን ነገር ያሳማዎታል። የተጻፈውን ነገር ካረጋገጡ በኋላ በወረቀት ላይ እንዲፈርሙ ይጠይቅዎታል። አዋቂ ከሆኑ ጠበቃ ወይም

ጓደኛ ወዘተ ሌላ ሰውን በቃለ መጠይቅ ላይ የማስታዘብ መብት የለዎትም። በይግባኝ ፕሮሴስ ላይ ግን ይፈቀድልዎታል።

አስቀድሞ በደምብ ዝግጅት አድርገው በቃለ መጠይቅ መገኘት ነው ወሳኝ የሆነው። ከቃለ መጠይቅ በፊት ዶክሜንቶችን ሁሉንም አዘጋጅተው የግል መግለጫ ወረቀትን እንደገና ያንብቡ። የሬፉጂ መርማሪ የርስዎን የግል መግለጫ ወረቀት አንብቦ እዚያ ላይ የተጻፈ ነገር እየተመለከተ ይጠይቅዎታል። በወረቀቱ ላይ ያልተጻፈ ነገር ወይም ከተጻፈው ነገር የተለየ ነገር የሚናገሩ ከሆነ በቂ የሆነ መግለጫ እንዲሰጡ ይጠይቅዎታል።

## 9)የጥገኝነት እውቅና እስከሚሰጠኝ ድረስ ምን ያህል ጊዜ ይፈጅብኛል?

እውቅና ቢፈቀድልዎም ባይፈቀድልዎም ውሳኔ ከመጣ ያሳውቁዎታል። ለምርመራ ምን ያህል ጊዜ እንደሚያስፈልግ ባጠቃላይ መንገር አይቻልም። ሰሞኑን የመጀመሪያ የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ውሳኔ በ6 ወር ያህል ይሰጣል እንጂ የይግባኝ ፕሮሴስ ይበልጥ እየተራዘመ ሆኖ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ የተወሰኑ ዓመታት የሚፈጅበት ኬዝም አለ።

## 10) እየተመረመረ ሲሆን ያመልካች አቋም ምን ዓይነት የሆነው ነው?

“ያጭር ጊዜ ቆይታ” ወዘተ የሆነ መኖሪያ ፈቃድ ኖሮዎት ባገልግሎቶ ጊዜው ውስጥ የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ያመለከቱ ከሆነ ውሳኔው እስከሚሰጥዎ ድረስ መኖሪያ ፈቃድዎን በተደጋጋሚ ማሳደስ ነው በኢሚግሬሽን የተለመደው። ባሁኑ ሰዓት ግን የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ካመለከቱ በኋላ አብዛኛውን ጊዜ “ልዩ እንቅስቃሴ” ወደሚለው መኖሪያ ፈቃድ ዓይነት ተቀይሮ ካመለከቱ 6ወር በኋላ ደግሞ ከኢሚግሬሽን የሥራ ፈቃድም ማግኘት ይችላሉ። መኖሪያ ፈቃድን ለማሳደስ ወደኢሚግሬሽን ቀርቦ የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ማመልከቻ ደረሰኝን ያሳዩዋቸው። ያገልግሎት ጊዜ ለማሳደስ ባንዴ የ4000ዬን ክፍያ ያስፈልጋል።

የሚያገለግል መኖሪያ ፈቃድ ሳይኖርዎት ያመለከቱ ከሆነ የጥገኝነት ጥያቄዎ ውድቅ ከተደረገብዎ በኋላ ሊታሰሩም ይችላሉ። የተወሰኑ ቅድመ ሁኔታዎችን የሚያሟሉ ከሆነ የጊዜያዊ ቆይታ ፈቃድ ማግኘት ይችላሉ እንጂ የጊዜያዊ ቆይታ ፈቃድ ትክክለኛ መኖሪያ ፈቃድ አይደለም። የጊዜያዊ ቆይታ ፈቃድ ካለዎ ከጃፓን አገር የማስወጣት ፕሮሴስ ይቆማል። ባሁኑ ሕግ መሰረት የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ አመልክቻለሁ በሚል ምክንያት መኖሪያ ፈቃድ ማግኘት አይቻልም። ሌላው ደግሞ ሳይታሰሩ የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ያመለከቱ ከሆነ ሳይታሰሩ ጊዜያዊ መልቀቂያ ሊፈቀድልዎም ይችላል። የጊዜያዊ ቆይታ ወይም የጊዜያዊ መልቀቂያ ፈቃድ ካለዎ በፖሊስም አያዙም አይታሰሩም። በተረፈ የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ፕሮሴስ እስከሚያልቅ ድረስ ኢሚግሬሽን ወዳገርዎ አስገድዶ አይልክዎትም።

## 11)ካመለከትኩ በኋላ በመንግስት የሚሰጠኝ እርዳታ አለ?

ለምግብ፣ ለቤት ኪራይ እና ለህክምና እርዳታ የሚውል የገንዘብ እርዳታና ለክፍል ቁጥር ወሰን ቢኖርም የመጠለያ እርዳታ ከRHQ（0120-925-357）ማግኘት ይችላሉ። ስልክ ደውለውለት ለማማከር ቀጠሮ ይያዙ።

## 12)ቢያመኝ ምን ባደርግ ይሻላል?

የጃፓን ሆስፒታሎች ከሞላ ጐደል የበሽተኛን መኖሪያ ፈቃድና አቅም ሳይመለከቱ የህክምና አገልግሎት ይሰጣሉ። ይህ አገልግሎት በነጻ ሳይሆን በኋላ እንዲከፍሉ ይጠይቁዎታል።

ከRHQ ከሚሰጥ እርዳታ ውጭ ከJAR（0120-477-472/03-5379-6003）ወይም ከISSJ（03-5840-5711）የህክምና ወጭ እርዳታ ለማግኘት ሊችሉም ስለሚችሉ ያማክሩዋቸው።

ከ6 ወር በላይ የሆነ መኖሪያ ፈቃድ ወይም የጊዜያዊ ቆይታ ፈቃድ ካለዎ ብሔራዊ ጤና ኢንሹራንስ መግባት ይችላሉ። ስለብሔራዊ ጤና ኢንሹራንስ የሚኖሩበትን ሰፈር ማዘጋጃ ቤት (kuyakusho, shiyakusho) ያማክሩ። ብሔራዊ ጤና ኢንሹራንስ ማለት አገር

የሚያስተዳድር የጤና ኢንሹራንስ ስርዓት ነው። ከገቡ የኢንሹራንስ ካርድ ይሰጥዎታልና ለህክምና የሚያስፈልግ ወጭም ይቀንሳል (ነገር ግን በነጻ አይደለም። የሚከፍሉት አብዛኛውን ጊዜ የህክምና ውጩ 30% ነው)። ኢንሹራንስ ለመግባት በገቢዎ መሰረት ክፍያ አለ።

ባስቸኳይ ህክምና ምክንያት በጣም ውድ የሆነ ክፍያ ከተጠየቁ የሆስፒታል የማህበራዊ አገልግሎት ሠራተኛን፤ RHQን፤ JARን ወይም ISSJን ያማክሩ። የመጀመሪያ ህክምና ነጻ ወይም ርካሽ የሚያደርግ የነጻ የርካሽ ህክምና ስርዓት ለመጠቀም ሊችሉም ስለምችሉ JARን ያማክሩ።

### 13) የልጆቼን ትምህርት እንዴት ላድርግ?

መኖሪያ ፈቃድ ሳይመለከት ከ1ኛ እስከ 9ኛ ክፍል ድረስ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት መማር ይችላሉ። በኤሌሜንተሪ ት/ቤትና በጁኒር ሃይስኩል ስለሚማሩበት መንገድ ደግሞ የሚኖሩበትን ሰፈር ማዘጋጃ ቤት (kuyakusho, shiyakusho) ያማክሩ።

### 14) የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ካመለከትኩ በኋላ ወደሶስተኛ አገር (ካናዳ፤ አሜሪካ፤ አውስትራሊያ ወዘተ) ለመሄድ እችላለሁ?

ጃፓን የሬፉጂ ስምምነት ስለፈረመች የጃፓን መንግስት ነው የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ማመልከቻ የሚያስፈጽም። በጃፓን ጥበቃ ሳይጠይቁ ለሶስተኛ አገር ቪዛ የሚያመለክቱ ከሆነ ወዳገሩ ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ሄደው ቅድመ ሁኔታዎችን ያረጋግጡ።

### በመጨረሻ …

ጥያቄ ካለዎ ወይም እርዳታ የሚፈልጉ ከሆነ JARን ያናግሩ።

### የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ አመልክቼ

እኔ የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ካመለከትኩ 4 ዓመት በኋላ ነው የሬፉጂ እውቅና የተሰጠኝ። የጃፓን መንግስት የጥገኙነት እውቅና የሚሰጥ ፕሮሴስ መስርቷል እንጂ በኔ ኬዝ እውቅና የተሰጠኝ አውቶማቲክ (ምንም ሳላደርግ) አይደለም። በመሰረቱ መንግስት ዝም ብሎ መወሰን የሌለበት ሲሆን የሬፉጂ ስምምነት የሚጠይቅ ቅድመ ሁኔታዎች የሚሟሉ ከሆነ የጥገኝነት እውቅና መስጠት አለበት። ነገር ግን ስቃይ ሊደርስብኝ ይችላል ብለው ቢያስቡም መንግስት እሱን ሳይስማማ የጥገኝነት እውቅና ላይሰጥዎትም ይችላል። ባደገኛ ሁኔታ ላይ እንዳሉና ጥበቃ እንደሚያስፈልግዎ መንግስትን የሚያስረዱት ራስዎ መሆንን ማወቅ ይገባል።

የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ፕሮሴሴ ብዙ ጊዜ ፈጀብኝ። ረጅም ጊዜ ለሚቆይ ምርመራና አስቸጋሪ ለሆነ ፕሮሴስ በቁርጠኝነቴ የምችለውን ሁሉ መስጠት ነው ወሳኝ የነበረው። ጠበቃዬ እንዳለኝ ከሆነ በእወነት የተፈጠረ ነገር አውቄ ደግሞ በፊት የደረሰብኝን ስቃይና ወዳገሬ ብመለስ የሚደርስብኝ ስቃይ ፍርሃት ለማስረዳት አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን መሰብሰብ የምችለው እኔ ብቻ ነኝ። ጠበቃዬና NGO ረድቶኛል እንጂ ወዳገሬ መመለስ እንደማልችል የጃፓን መንግስት ለማስረዳት ወሳኝ የነበርኩት እኔ ነኝ። ለፕሮሴስ ጊዜ ከመፍጀት በተጨማሪ ሌላ ችግርም ስለነበረ ይበልጥ ችግር በዛብኝ። እኔ በጃፓን የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ከማመልከቴ በፊት የሥራ ፈቃድ ስላልነበረኝ ካመለከትኩ በኋላ ሁሌ መሥራት አልችልም ነበረ።

ከዶክሜንቶች ውስጥ የግል መግለጫ ወረቀት በጣም ቁም ነገር ነው ብዬ አስባለሁ። እኔ ሁኔታው ምን ያህል የባሰ ሆኖ ለማጥቃት በኔ ላይ ትኩረት እንደሚሰጡ ለመግለጽ ሞከርኩ። ወዳገሬ ብመለስ ሊደርስብኝ የሚችል ነገርን ተጨባጭነት ያለውን ምሳሌ ጠቅሼ ለመግለጽ ጥረት አደረግኩ። ከቃለ መጠይቅ በፊት የግል መግለጫ ወረቀቴን ማንበብ አልረሳሁም። በቃለ መጠይቅ ተመሳሳይ የሆነ ጥያቄ በተደጋጋሚ ተጠየቀ። እኔ ለጥያቄው እውነትን በተቻለ መጠን ተጨባጭነት ባለው መልክ መለስኩ።

ከመጨረሻ ቃለ መጠይቅ ከ1 ዓመት በኋላ በኢሚግሬሽን ተጠርቼ ለኔ የጥገኝነት እውቅና እንደተፈቀደልኝ የሚገልጽ ወረቀት ተሰጠኝ።

# ተጨማሪ I የጃፓንኛ ቃላት ፍች ዝርዝር

እኔ ሬፉጂ ነኝ። -- *watashi wa nanmin desu*

ወዳገሬ መመለስ አልችልም። -- *watashi wa jibun no kuni ni kaeremasen*

የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ለማመልከት እፈልጋለሁ። -- *nanmin nintei shinsei o shitai desu*

ስቃይ ደርሶብኝ ነበረ። - *watashi wa hakugai saremashita*

አደገኛ ነው። -- *kiken desu*

ይግባኝ〈የጥገኝነት እውቅና ካልተፈቀደልዎ〉 -- *igi moushi-tate*

ማመልከቻ ፎርም -- *shinsei youshi*

ካገር የማስወጣት ፕሮሴስ -- *taikyo kyousei* or *kyousei soukan*

እስረት -- *koukin* or *shuuyou*

ቤተሰብ -- *kazoku*

መንግስት -- *seifu*

ሰብአዊ መብት -- *jinken*

የሰብአዊ መብት ረገጣ -- *jinken shingai*

የኢሚግሬሽን ቢሮ -- *nyuukoku kanri-kyoku* or *nyuukan*

ጠበቃ -- *bengoshi*

ስቃይ -- *hakugai*

የፖለቲካ ፓርቲ -- *seitou*

ዘር -- *jinshu*

ደረሰኝ〈የማመልከት〉-- *juri-hyou*

ሬፉጂ -- *nanmin*

የሬፉጂ መርማሪ -- *nanmin chousa-kan*

የሬፉጂ እውቅና -- *nanmin nintei*

የሬፉጂ እውቅና ፕሮሴስ -- *nanmin nintei tetsuzuki*

የክልል ኢሚግሬሽን ቢሮ -- *chihou nyuukoku kanri-kyoku*

የሬፉጂ እውቅና አለመገኘት - *nanmin fu-nintei*

ሃይማኖት -- *shuukyou*

ቶክዮ ኢሚግሬሽን ቢሮ -- *Tokyo nyuukoku kanri-kyoku* or *Tokyo nyuukan*

ቶርች -- *goumon*

ፍርድ〈የፍርድ ቤት〉-- *saiban*

UNHCR -- *kokuren nanmin koutou benmu-kan* or simply UNHCR

# ተጨማሪ II አድራሻ ወዘተ

UN High Commissioner for Refugees (UNHCR) Representation in Japan
Wesley Center, 6-10-11 Minamiaoyama, Minato-ku, Tokyo, Japan
〒107-0062 Tel: 03-3499-2011 Fax: 03-3499-2272 Office hours: 10:00 AM – 18:00 PM
http://www.unhcr.or.jp

Refugee Assistance Headquarters (RHQ), Foundation for the Welfare and Education of the Asian People (FWEAP)
5-1-27 Minami-Azabu, Minato-ku, Tokyo, Japan
〒106-0047 Tel: 0120-925-357/03-3449-7011 Fax: 03-3449-7016

- Kansai Branch
  Nissei Kobe Ekimae Bldg., 11th Floor, 2-1-18 Nakamachi-dori, Chuo-ku, Kobe City, Hyogo, Japan
  〒650-0027 Tel: 0120-090-091/078-361-1700 Fax: 078-361-1323

Immigration Bureaus

- Tokyo Regional Immigration Bureau
  5-5-30 Konan, Minato-ku, Tokyo, Japan
  〒108-8255 Tel: 03-5796-7111

  Yokohama District Immigration Office
  10-7 Torihama-cho, Kanazawa-ku, Yokohama City, Kanagawa, Japan
  〒236-0002 Tel: 045-769-1721

  Narita Airport District Immigration Office
  Narita Airport Second Terminal Bldg., 6th Floor, 1-1 Furugome, Narita City, Chiba, Japan
  〒282-0004 Tel: 0476-34-2211

- Osaka Regional Immigration Bureau
  1-29-53 Nankou Kita, Suminoe-ku, Osaka City, Osaka, Japan
  〒559-0034 Tel: 06-4703-2190

  Kansai Airport District Immigration Office
  1 Senshu-Kuko-Naka, Tajiri-cho, Osaka, Japan
  〒549-0011 Tel: 072-455-1457

  Kobe District Immigration Office
  Kobe Local Joint Government Bldg., 29 Kaigan-dori, Chuo-ku, Kobe City, Hyogo, Japan
  〒650-0024 Tel: 078-391-6378

- Nagoya Regional Immigration Bureau
  5-18, Shoho-cho, Minato-ku, Nagoya City, Aichi, Japan
  〒455-8601 Tel: 052-559-2120

- Hiroshima Regional Immigration Bureau
  2-31, Kami-hacchobori, Naka-ku, Hiroshima City, Hiroshima, Japan
  〒730-0012 Tel: 082-221-4412

- Fukuoka Regional Immigration Bureau

Fukuoka Airport Domestic Flights Terminal #3, 778-1 Shimo-usui, Hakata-ku, Fukuoka City, Fukuoka, Japan
〒812-0003 Tel: 092-626-5151

**Naha District Immigration Office**
Naha First Local Joint Government Bldg., 1-15-15 Higawa, Naha City, Okinawa, Japan
〒900-0022 Tel: 098-832-4186

- **Sendai Regional Immigration Bureau**
  Sendai Second Legal Affairs Joint Government Bldg., 1-3-20 Gorin, Miyagino-ku, Sendai City, Miyagi, Japan
  〒983-0842 Tel: 022-256-6076

- **Sapporo Regional Immigration Bureau**
  Sapporo Third Joint Government Bldg., Odori-nishi 12 Chome, Chuo-ku, Sapporo City, Hokkaido, Japan
  〒060-0042 Tel: 011-261-9658

- **Takamatsu Regional Immigration Bureau**
  Takamatsu Legal Affairs Joint Government Bldg., 1-1 Marunouchi, Takamatsu City, Kagawa, Japan
  〒760-0033 Tel: 087-822-5851

ይህንን መጽሔት የሚመለከት ጥያቄ ካለዎ መቼም ይጠይቁን።


## Japan Association for Refugees

Daisan Shikakura Building 6F, 1-7-10, Yotsuya, Shinjuku-ku, Tokyo, Japan
TEL (toll-free line for refugees/ asylum seekers): 0120-477-472
TEL (hotline for refugees/ asylum seekers): 03-5379-6003
Fax: 03-5379-6002
Email: info@refugee.or.jp

http://www.refugee.or.jp


# የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ ለሚያመለክቱ ሰዎች የሚሰጡ ምክሮች


በJAR በፈረንጆች 2013


JAR የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ አመልካቾችን የሚመለከት ምርምር ያደርጋል። በርስዎ ኢንፎርሜሽን ለምርምር ሊጠቀምበትም ይችላል። የምርምር አላማ የጥገኝነት እውቅና ጥያቄ አማልካቾች ፍላጐትና የሚገኙበትን ሁኔታ በማወቅ ለሬፉጂዎች የተሻለ ሁኔታ መፍጠር ነው። በዚህ ምርምር የተገኘ የግለ ሰብ መረጃ ለሌላ ሰው አይሰጥም። ሌላው ደግሞ በኋላ በሚጻፍ የምርምር ሪፖርት ላይም የግለ ሰብ ስምንና ማንነቱን ለማወቅ የሚያስችል ኢንፎርሜሽን አይጋለጥም። JAR ደግሞ ምርምርና ትንታኔ ሲያደርግ በጥገኝነት እውቅና ጥያቄ አመልካች ላይ ማንኛውም ዓይነት ጉዳት አይደርስባቸውም ብሎ ይምላል።